# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቿፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 27 ሕዳር 11 2001 ዓ.ም


**አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !**

## "ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ይኖራል ብዬ አላምንም"አና ጎሜዝ

*የተከበሩ አና ጐሜዝ በአውሮፓ ፓርላማ የሶሻሊስት ቡድን አባል እና በ1997ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ ወቅት የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን ኃላፊ የነበሩ ሲሆን፤ ።ባለፈው ሳምንት ካቀረብነው ቃለ ምልልስ ተከታይ ክፍል ለዛሬ የመጨረሻውን እነሆኖር፡ ሶማሊያን በተመለከተ፥ በ2006 የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች አይ.ሲ..ዩ. የሶማሊያን የሽግግር መንግስት እየተቋቋመ መሄዱንና ወደፊት ደግሞ እንደ ኦጋዴን ያሉትን የኢትዮጵያ ግዛቶች ለመውሰድ ዕቅድ እንዳለው ዘግበው ነበር። የተባበሩት መንግስታትም ኤርትራ አይ.ሲ..ዩን ትደግፋለች ብሎ ሲወቅሳት፣ አይ.ሲ..ዩ.ን ደግሞ ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት አለው ብሎ ወንጅሎታል፤ አንዳንድ ተመልካቾች ግን የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ ውስጥ የአፍራሽነት ሚና ተጫውቷል ብለው ሲወቅሱት፣ አሁን ደግሞ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች የሆነው ሂውማን ርይትስ ዋች የኢትዮጵያ ጦር የጦር ወንጀል ፈጽሟል ብሎ እየወነጀለው ነው። የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባቱ ትልቅ ስህተት ፈጽሟል?*

**አና ጐሜዝ፡** አዎን፤ ደግሞም የኢትዮጵያ እና የሶማሊያ ህዝብ በየቀኑ እየከፈሉ ያሉበት ትልቅ ስህተት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ...ደም መፋሰስ ሆኗል፣ አይን ያወጣ ግድያ በሶማሊዎችና በኢትዮጵያውያን ላይ ተፈጽሟል። ያ ደግሞ ወደፊት በኢትዮጵያና በሱማሌ ህዝብ መሃል ቂም ሊፈጥር ይችላል። አቶ መልስ ዜናዊ አይኖችን ከራሱ ላይ ለማስነሳትና በቡሽ አስተዳደር እራሱን ለማስወደድ ሲል ሱማሊያ የሚሄደው ሽብርተኛነትንና አክራሪነትን ሊዋጋ እንደሆነ ለማስመሰል ሞከረ። እኔ እንደሚመስለኝ፣ እንደሌሎቹ ተመሳሳይ ጦርነቶች ሁሉ የለኮሰው እሳት መልሶ ያቃጥለዋል። እንደምናየውም፣ ይሄ ጦርነት እክራሪዎቹን የበለጠ አጠንክሯቸዋል፣ የኢትዮጵያም ጦር ፈጽሞ ካገሪቱ ውስጥ ሊያወጣቸው አልቻለም። ይህ በንዲህ እንዳለ፣ በሶማሊያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ደም መፍሰስ የማይታሰብ ነው። የተባበሩት መንግስታትም፣ ከዩናይትድ ስቴትስ ጀምሮ ካንዳንድ አይን አውጣ አባለ-አገራቱ ባህሪ የተነሳ ስለደከመ፣ የኢትዮጵያ ጦር ከሶማሊያ እንዲወጣ የሚያግዝ የሰላም አስጠባቂ ሃይል ወደ ሶማሊያ ሊልክ አልቻለም። እናም የኢትዮጵያ ጦር እዚያው ተቀርቅሮ መቅረቱ ነው፤ ያ ሲሆን ደግሞ ሂውማን ራይትስ ዋች እና አምንስቲ ኢንተርናሽናል የሰበሰሰቧቸውን አይነቶች የጦር ወንጀሎች መፈጸሙን ይቀጥላል። አየተከሰተ ስላለው ነገርና የተቀረው ዓለምና እራሱን ሁለተኛ አድርጎ የዩ.ኤስ. ፖሊሲ እንዲቀጥል የፈቀደው የአውሮፓ ሕብረት ጉዳዩን ስለዘነጉበት ሁኔታ እጅግ በጣም አዝናለሁ። በሶማሊያ ያለውን ክፉ ቀውስ መጨረሻ አይተናል ብዬ አላምንም፤ የበለጠ መከራ በሶማሊዎች፣ በኢትዮጵያኖች እና ባካባቢው ሕዝብ ላይ ገና ይመጣል።

**የሮ፡** ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጣልቃ ባትገባ ኖሮ አይ.ሲ..ዩ. እና አል ሸባብ የሽግግር መንግስቱን ወደሚደግፉ አካባቢዎች የሚያደርጉትን ግስጋሴ ያቆሙ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ያሳዩትን አደገኛነት ያቆሙ ነበር ብለው ያምናሉ?

**አና ጐሜዝ፡** እንግዲህ፣ የሽግግሩ መንግስት ተርት ሆኗል፤ እኔ እስከማውቀው ድረስ አይ.ሲ..ዩ. ከምንም ጊዜ በላይ ጠንክሯል። በተጨማሪም የሶማሊያ መፍትሄ የሚንተራሰው ሁሉም የሶማሊያ ወገኖች ባንድ ላይ ሲሰባሰቡና ልዩነቶቻቸው ለመፍታት ሲሰሩ ነው፤ ለዛም ከውጪ በመጡ ታዛቢዎች ሊታገዙ ይችላሉ። የተባበሩት መንግስታት፣ በኦባማ የሚመራው የወደፊቱ የዩ.ኤስ. አስተዳደር እና አውሮፓ በዚህ ውስጥ ወደ ፊት ሚና ሊኖራቸው ይችላል። ይህ አሁን ሲከሰት አላይም። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስር ያለችው ኢትዮጵያም በሶማሊያ ውስጥ አዎንታዊ ሚና ስትጫወት አላይም። ከዚህ ወረራ እና ከነዚህ የጦር ወንጀሎች በኋላም፣ ኢትዮጵያ ሶማሊያን በተመለከተ የባሰ በከፋ ሁኔታ ውስጥ ነው የምትሆነው። ወደ ፊት የሚመጣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግስት አሁን የተፈጠሩትን ቁስሎች ይፈውሳል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

(ወደገጽ 4 ዞሯል)

## በሌላው ሁሉ ተስፋ ሊቆረጥ ይችላል።

### በኢትዮጵያችን ግን ተስፋ አይቆርጡም

ሃገራችን ስላላችበት ጭንቅና መከራ ህዝባችን ስለሚኖርበት የምድር ሲኦል፣ ብዙ ተብሏል። የወያኔ ኢህአዴግ መሪዎች የመለስ ዜናዊንና የኩባንያውን ጸረ-ኢትዮጵያዊነት፣ በሃገርና በወገን ላይ የፈጸሙትን በደልና ግፍ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጠንቅቆ ያውቀዋል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚፈልገውና የሚመኘው ነገር ቢኖር በእዛች ደሃና መከረኛ ሃገራችን ላይ ሰላም ሰፍኖ፣ የህዝብ መብት ተጠብቆ የዜጎች አንድነትና የሀገርና ህልውና ተከብሮ፣ በአለም እያዋረደን ካለው የድህነት፣ ችጋርና የስደተኛነት መለያችን መገላጋል እንደሆነ እናውቃለን።

ይህ በጎ የህዝብ ምኞት እንዲሰምር ብዙ ኢትዮጵያውያን ህይወታቸው፣ ሃብት ንብረታቸውን፣ የተረጋጋ ኑሮዋቸውን፣ የቤተሰቦቻውን ደህንነት ገብረዋል። እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን ከተከመረባት ዘረኛና አምባገነነናዊ ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይል ለመገላገል ቆርጬ ተነስቻለሁ ለሚል ድርጅት የሃገራችን ዜጎች ያላበረከቱት ድጋፍ፣ ያልተመኙት በጎ ምኞት የለም። በተለያዩ ምክንያቶች ድርጅቶች ሲነሱ ሲወድቁ፣ ገበናቸው ሲጋለጥ፣ እንኳን ህዝብና ሃገርን የሚያክሉ ታላላቅ ነገሮች ነጻ የሚያደርግ ትግል እንቅስቃሴ ማደራጀት ቀርቶ እርስ በርሳቸው ተስማምተው መሄድ የማይችሉ ስብስቦች መሆናቸው ሲታይ፣ የህዝብ ስሜት በሃዘን ሬት ሲበከል አይተናል። አደራና ቃል የማያከብሩ፣ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ለህዝቧ የመከራ ቀን ማሳጠሪያ ህዝብ ተቸግሮ በአመኔታ የሰጣቸውን ጥሪት ቀኑ መሸቶ የሚበላ የማይገኝ እንደሚመስለው ጅብ ተስገብግበው ውጠው ያለምንም ሃፍረት አይናቸውን እያጉረጠረጡ በህዝብ ውስጥ ሲሹለኮሉ በማየት አንጀቱ የበገነው ብዙ እንደሆነ እናውቃለን።

የሃገር ጉዳይ ሆነና አንዱ ድርጅት ሲከዳ፣ ቃሉን ማክበር ሲያቅተው በሌላው አዲስ ቃል ኪዳን በሚሰጥ፣ በሌላ ጥሩ ተናጋሪና ጥሩ ጸሃፊ ባለው ድርጅት እየተተካ አዲሱም እንዳሮጌዎቹ ያንኑ የቆየ የክህደት ቡቱቶ ሲላበስ፣ በህዝብ እምነትና በድርጅቶች ከህደት መሃከል ያለው የአዙሪት ቀለበት ሳይሰበር እዚህ ደርሰናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱም ሆነ ሃገሩ ያሉበት አስቸጋሪና ፈተኛ ሁኔታ እንዲቀየር ይፈልጋል። ይህንን ለውጥ ግን በተናጠል ማድረግ እንደማይችል፣ ለውጡን የሚደራጅና የሚመራ ድርጀት እንደሚያስፈለገው ይረዳል። የድርጅት ጉዳይ ደግሞ ደጋግሞ የህዝቡን ቀልብ የሚስበው ለእዚህ ነው። ድርጅት ለለውጥ አስፈላጊ በመሆኑ እንጂ ህዝብ እንደታዘባቸው የተለያዩ ድርጅቶች ማንነትና ድርጊት ቢሆን ኖሮ የድርጀት ጉዳይ ሲነሳ ጆሮዎቹን በጣቶቹ ደፍኖ አትድረሱብኝ ሊል ይችል እንደነበር እናውቃለን።

ይሁንና በእዚህ አስከፊ ክፉ ዘመን፣ ከረሃቡም ከችግሩም ከግድያውና ከእስራቱም በላይ፣ የኢትዮጵያችን ህልውና፣ የአገዛዙን ስልጣን በያዙ ጸረ-ኢትዮጵ ሃይሎች ለከፍተኛ አደጋ በተጋለጠበት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በፖለቲካ ድርጅቶችና በፖለቲካ ሰዎች ላይ ተስፋ መቁረጥ በኢትዮጵያ ላይ ተስፋ መቁረጥ አድርጎ ስለሚያየው ጣቶቹን ጆሮው ጫፍ ላይ አስቀመጠ እንጂ አልሰማም ብሎ አልጠቀጠቃቸውም። አሁንም፣ ፈራ ተባ እያለ ቢሆንም አዲስ ቃል ኪዳን ለሚገቡ፣ አዲስ ራእይና ቁርጠኛነት አለን ለሚሉ ድርጅቶች ጆሮውን ለማዋስ እድሉን ለመስጠት ከመሞከር አልቦዘነም። እናውቃለን።(ወደገጽ 2 ዞሯል)

## ርእሰ አንቀጽ

# አፍንጫችንን ሰንገንም ከዘረኛነት ክርፋት ማምለጥ ካልቻልን፣ ምርጫችን ዘረኛነትን ከአካባቢያችን መጥረግ ብቻ ነው

ምናልባት የወያኔን ዘረኝነት የሚጠራጠሩ ካሉ ሁለት ክስተቶችን ብቻ እንዲያጤኑ እንጋብዛቸዋለን ። የሰራዊቱን የከፍተኛ መኮንኖች የብሄረሰብ ተዋፅኦ እና በውጪ ሃገር የትምህርት ዕድል የሚሰጣቸውን ተማሪዎች የብሄረሰብ ስብጥር። ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ ዝም ብሎ የዘር መድልኦ ነው፣ ወይም በተለመደው አጠራሩ አፓርታይድ ነው ማለቱ ይቀላል ። ሌላ ስም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው። እኛም በቀላሉ አይደለም እንዲህ አይነት ውንጀላ የምናደርገው። በጉዳዩ አልቅሰንበት፣ አውጥተን አውርደን፣ ለወራት ዝምታን መርጠን፣ በመጨረሻ ግን፣ ክፋትን ከመሸሽ መጋፈጡ ይሻላል ብለን ይፋ ያደረግነው ጉዳይ ነው ። ጉዳዩን ትኩረት ስንሰጥም፣ ወያኔ ቆሜለታለሁ የሚለው ብሄረሰብ አባላትም፣ ይህን ኢፍትሃዊና ሃገር አውዳሚ ጉዞ አብረውን ይብቃ ለማለት፣ የተመዛዘነ አእምሮም ሆነ ዜጋዊ ድፍረት ይኖራቸዋል ብለን ስለምናምን ነው ። "በስማችን በወንድሞቻችንና በሃገራችን ላይ ግፍ ሲሰራ በዝምታ አናይም" ብለው ከጎናችን እንደሚሰለፉ ስለማንጠራጠር ነው ።

በአሁኑ ሰአት በወያኔ በቁጥጥር ስር ባለው የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ከጄኔራል ከሁለቱ በቀር ሁሉም ጄኔራሎች የትግራይ ብሄረሰብ አባላት ናቸው ። ከቺፍ ኦፍ ስታፉ ከጄኔራል ሳሞራ ጀምሮ፤ ብንወርድ፣ ሁሉም በጄነራልነታቸው የያዙት ቦታ ከቀሩት ሁለቱ ጀኔራሎች የተለዩ ቁልፍ ቦታዎችን ነው። ሙሉ በሙሉ ከአንድ አካባቢ የተለቃቀሙ ናቸው ። በደግነት፣ በወያኔ የትጥቅ ትግል ዘመን ልምድና ችሎታ ያዳበሩት እነዚሁ ስለሆኑ፣ ምናለበት ወታደራዊ መሪ ቢሆኑ የሚል ክርክር ማንሳት ይቻላል ። ግን ይህ አገዛዝ ትናንት የተመሰረተ ስርአት አይደለም ። 18 አመታት አስቆጥሯል ። ቀናነት ቢኖረው ከሌሎቹ የኢህአዴግ አባላትም መሃል፣ ከኦሮሞዎቹ፣ ከአማራዎቹ ብዙ ጄኔራሎችን ማሰልጠንም ሆነ መሾም ነበረበት ።በባድመ፣ በፆረና፤ በኦጋዴን፤ በሞቃዲሾ የዘመቱትና የተዋጉትና ያዋጉት የመለስ ቅምጦች ብቻ እንዳልሆኑ እኛም ሰራዊቱም ያውቀዋል ። እንዲያውም፣ ወያኔ ራሱ ጀምሮት የነበረውን የጦር መኮንኖቹን ብሄራዊ ተዋፅኦ የመጠበቅ ፖሊሲ፣ ለመቀልበስ የተገደደው ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ መሆኑንም እናውቃለን ። ወያኔ መንግስት ሲሆን ሶስት ትግሬ፣ ሶስት አማራ፣ ሶስት ኦሮሞ ጄኔራሎችን በመሾም ነበር "የብሄሮች እኩልነት" አስጠባቂ ነኝ ብሎ ራሱን ያሞካሽ የነበረው ። ሆኖም የግንቦት 97ን የምርጫ ውጤት አልቀበልም ብሎ ሞገደኛ መሆን ከመረጠ በሗላ ግን፣ አዳዲስ የትግሬ ጄኔራሎችን ሲሾም፣ አራቱን የአማራና ትግሬ ጄኔራሎች አወረደ ። የምርጫውን ውጤት ህዝብ ለለውጥ የነበረውን ጥማት ለማርካት ያደረገው ዴሞክራሲአዊ ሙከራ አድርጎ ከማየት ይልቅ፣ አማሮችና ኦሮሞዎች በህብረት አገዛዙን ለመጣል አደረጉት ሴራ አድርጎ ተገነዘበው ። የራሱንም ጥላ ማየት ያስደነብረው ጀመር ። ስለሆነም ታዛገፑ የሆኑ ጄኔራሎቹን እንኳ ማመን አልቻለም ። ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ተደረገውን ትግል፣ በዘር ፍጥጫ መለወጥ ይመቸኛል በሚለው ስሌቱ ቀጥሎበት፣ ይሄው ዛሬ ካለንበት የገደል ጫፍ ላይ ደርሰናል ።

ወያኔ በወታደሩ ውስጥ ጀመረውን ዘረኛ አንድ ወጥነት፣ እጅግ በጎለበተ መልኩ በሌሎቹም መስኮች ይገፋበት ጀመር ። የዚህ ዘረኛ ፖሊሲ ሰለባ ከሆኑት መሃል፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ናቸው ። በተለይ የውጪ ትምህርት ዕድል፣ ለትግራይ ተማሪዎች ብቻ የተተወ ሆኖአል ። አንድ በቅርቡ አውሮፓ፣ ኔዘርላንድስ ውስጥ የተላኩት ተማሪዎች የብሄረሰብ ተዋፅኦ የወያኔን ምንነት የሚናገር ነው።አገናዋ በሚባለው ኮሌጅ ውስጥ ለድህረ-ምረቃ ዲግሪ ከተላኩት 55 ተማሪዎች መሃል 50 የሚሆኑት ከትግራይ ናቸው። ሁለት ነገሮችን በፅሞና እንድናይ ወያኔ ይጋብዘናል ። በአንድ በኩል ቅስማችን ለመስበር ይችል እንደሁ ሊፈታተነን "ምን አባታችሁ ትሆናላችሁ?" ብሎ ዐይናችን ውስጥ መትፋቱ ሲሆን፣ ሁለተኛውና ያፈጠጠው ሃቅ ግን እንደ ሲሪያው አሳድ፣ እንደ ኢራቁ ሳዳም፣ ከቤተሰብ ትስስር ባላለፈ ውሁዳዊ አገዛዝ ለመቀጠል እችላለሁ፣ ይገባኛልም ብሎ መወጠኑን ነው ። ትፋቱንስ ግዴለም እንጠርገዋለን እንል ይሆናል፣ ለአመታት እየተተኩ ሊገዙን የሚችሉ መሃይሞችን ባህርማዶ ድረስ ልኮ ለማሰልጠን መቁረጡን ስንረዳ ግን በሃገራችን ላይ ባለቤቶች ነን ማለት ይቻለናል? ግንቦት ሰባት፣ ዳግም እብሪትና ገሃነማዊ ክፋትን ከመጋፈጥና ከመርታት ውጪ ምንም ምርጫ የለንም ይላል? እርስዎስ? ያልዎትን ይወርውሩ? እምቢ ለዘረኛ አገዛዝ ይበሉ ። ወያኔ ለኢትዮጵያ የማይመጥን አውር መሆኑን አውቀው በፀሎትዎም፣ በህልምዎም፣ በዕውኖም ስለኢትዮጵያ ተስፋ ይጨነቁ ። "ሃገር የሞተ ቀን በማን ይለቀሳል" ነው ነገሩ ። መለስ ዜናዊ በዘረኝነት ጭስ ኢትዮጵያችንን አፍኖ፣ ማሯን ሊቆርጥ፣ ንግስቷን ሊገድል፣ ገበናችንን ኢትዮጵያ የተባለች የንብ ቀፎአችንን ሊደረምስ መቁረጡን እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ከልባችን እንያዛቸው ። የኢትዮጵያ ንቦች መፈተኛቸው ቀን ደርሷል፣ ቀፎአቸውን አስነክተው የት ሊገቡ? የት ሊጠጉ? ከማ ሊያድሩ? መራሩ ሃቅ ይሄው ነው ። እንግዲህ መላው ሃገር አይሰደድ? ማንቁርት ለማንቁርት ተያይዞ ይሞታል እንጂ ። ዕጣችን አምርሮ መታገል፣ በምሬታችንም መጠን የሚጣፍጥ ድል መቀዳጀት ከሆነ፣ ፈጣሪያችን ለኛ የጋገረውን እንጎቻ ሌላ እንዳይበላው እሙን ነው ። አይዞን ።

## በሌላው ሁሉ ተስፋ ሊቆረጥ...

ከገጽ 1 የዞረ

ይህንንም ብለን ግን በድርጀቶች መሪዎች ድክመት፣ መዝረክከረክና ማንአለብኝነት የባከነው የህዝብ ህይወት፣ ሀብት፣ እውቀትና ጉልበት የተጎዳው ቀናና በጎ ስሜት በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ግንቦት7 የተመሰረተው፣ እንዲህ አይነቱ ስሜት በህዘብ ውስጥ መኖሩን እያወቀ ነው። በእኛም ውስጥ በህዝብ ውስጥ የሚነሳው ስሜት ተነስቶ ነበር። ‹‹ተሰባስበን ለመስራት ያደረግነው ሙከራ ከሽፏል። የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ መግባት፣ የፖለቲካ ድርጅት መሰርቶ መንቀሳቀስ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው። ትርፉ ውሎ አድሮ በራስና በቤተሰብ ላይ ከሚያስከትለው ጭንቅና መከራ፣ ህዘብን እንዳለፉት ድርጅቶች እኛም በምናሳየው ድክመት ማስቀየም ነው።›› ብለን በመተከዝ አሰላስለናል። ይሁንና እኛም እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ተሰፋ እንዳንቆርጥ ያደረገን፣‹‹ አባት የሞተ እንደሁ በሃገር ይለቀሳል ሃገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል›› በማለት እጅግ አሽቸጋሪ ፈተናዎች አልፈውና መስዋእትነት ከፍለው ይችን ውድና ክቡር ሃገር ለኛ ያስተላለፉ ቀደምቶቻችን ጨኸት ከየወደቁበት ፈፋና ፈረፈር በረሀና ጫካ ተራራና ሸለቆ ዱርና ገደል እያስገመገመ ስለሰማነው ነው። ሀገርን የሚያክል ነገር፣ በተለይ ኢትዮጵያን የሚክል፣ ዙሪያችን እንደምናያቸው ሃገሮች ማንም ጠፍጦ ያልሰራትን ሃገር፤ ትውልድ በደሙ ዋኽቶ ያቆያትን ምድር፤ መለስ ዜናዊን ለመሰለ በጸ- ኢትዮጵያነት በቀል ለሚንቀሳቀስ ከሃዲ አስረክበን መቀመጥ የማይቻል የማይታሰብ ስለሆነብን ነው።

ትግሉ ሃገርን የማዳን ብቻ ሳይሆን እራስንም ልጆቻችንም ቤተቦቻችንም ነጻ ለማውጣት የሚደረግ መሆኑን እያወቅን በተለይ እኛ ግንቦት7ን የመሰረትነው አባላት ሌላ ነጻ አውጪ ጠባቂዎች ሆነን ብንገኝ አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን በሞራል ወንጀል የሚየስጠይቅ መሆኑን በማወቃችን ነው እኛም ምርጫችንን በትግሉ መቀጠል ብቻ ያደረግነው። ይህ በመሆኑ ነው፣ ስለወያኔ/ኢህዴግ ማንነት ያለን እውቀት፣ ወያኔን/ኢህአዴግን ለመታግል ከሚያስችለው ህዝብን በስፋት ለማንቀሳቀስ ካለን ተመክሮዋችን፣ ማሰባሰብ ከምንችለው በዘመናዊነትና በእውቀት የታጠቀ የሰው ሃይል፣ በጥናትና ምርምር በተደገፈ የትግል አቅጣጫና መገንባት በምንችለው የደርጅት አቅም፣ መንድፍ በምንችለው የተጋድሎ ታከቲክና ስትራተጂ፣ ሁላችንምና ሀገራችን አዋርዶ ለመግዛት የሚፈልገውን እብሪተኛ አገዛዝ ለማስወገድ ባላን እልህ፣ በተለይ ከነበርንበት ድርጅትና ከሌሎችም ድርጅቶች ጥፋቶች በሚገባ ከቀሰምነወ ትምህርት ተነስተን፣ የህዝብን ስሜት ማደስ፣ ምኞቱን ማስፈፈጸም የሚቸል ንቅናቄ ማቆም፣ ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች በነጻነትና በእኩልነት የሚያስተናግድ አንድነታቸውን ለማስጠብቅ አልሞ የተነሳውን ራእያችንን ማስፈጸም አያቅተንም ብለን ነው፤ የግንቦት 7ን ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄን ያቆምነው።

በሩቁና በቅርቡ በሆነው ተከፍቶ በሃገሩ ላይ ተስፋ እንደማይቆርጠው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ እኛም ምንም አይነት ፈተና ቢገጥመን በሃገራችን ላይ ተስፋ አንቆርጥምና ከወደቅንበት ቀሻሻ ስፍራ አብሮን የተነሳውን ትቢያ አራግፈን በድፍረት ቆመናል። ብዛታችንን፣ የትግላችን ፍትሃዊነትና የአላማችን ርቱእነት፣ ድል አድራጊነታችን አስቀድሞ የተነበየው ነውና እንደ ቀደምቶቻችን ሃገራችንን በመታደግ ለልጅ ልጆቻችን፣ ለቤተሰቦቻችንና ለትውልድ የሚተላለፍ አኩሪ ታሪክ በጋራ እንስራ እንላችኋለን።

---

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ሶማሊያ:ደርሶ:መልስ (ኤፍሬም:ማዴቦ)

ምከረዉ:ምከረዉ:እምቢ:ካለ:መከራ:ይምከረዉ:ይሉ:ነበር:አባቶች:ሲተርቱ፤የዛሬዉም:ትዉልድ:የማይሰማና:የማይመከር:ሰዉ:ሲያጋጥመዉ:የሚተርተዉ:ተረት:ነዉ::የሚወዱት:ጓደኛ:ወይም:ወዳጅ:ደጋግሞ:ሲያጠፋ:በተደጋጋሚ:ይመከርና:ጭራሽ:አልሰማ:ካለ:እስኪ:ከጥፋቱ:ይማር:ተብሎ:ይተዋል፤ነገር:ግን:አገርን:ያክል:ትልቅ:ነገር:የሚመሩ፣ህግ:የሚያረቅቁና:ህግ:የሚተረጉሙ:ሰዎችየቀኑ:ለ180መት:ትልልቅ:ጥፋት:ሲያጠፉ:ምን:ይደረጋል?

አዎን፤ለታፈነና:ሰብዓዊ:መብቱን:ለተቀማ:ህዝብ:ግራ:የሚያጋባ:ጥያቄ:ይመስላል:ነገር:ግን:ወያኔ:የሚበድለዉ:ህዝብን:የሚያጠፋዉ:ደግሞ:አገርን:ነዉና:ምን:መደረግ:አለበት:የሚለዉ:ጥየቄ:በአፋጣኝ:መመለስ:ይኖርበታል::ባለፉት:17 0መታት:ወያኔ:በሉዓላዊነት፣ጥየቄ፣በሰብዓዊ:መብት:ጥየቄ፣በዲሞክራሲና:በፍትህ:ጥያቄ:ከኢትዮጵያ:ህዝብ:ጋር:የተስማማበት:አንድም:ግዜ:የለም::በታህሳስ:1999 መለስ:ዜናዊ:ጦሩን:ወደ:ሶማሊያ:ሲያዘምት:ያልጮኸ:ያልመከረዉና:እግዚኦ:ያላለ:ኢትዮጵያዊ:አልነበረም::ህዝብን:የሚሰማ:ጆሮና:አርቆ:የሚያስተዉል:ልቦና:አብሮት:ያልተፈጠረዉ:መለስ:ዜናዊ:ግን:የተለመደ:ዉሸቱን:በመደርደር:ጆሮ:ዳባ:ልበስ:ብሎ:ጦሩን:ወደ:ሶማሊያ:አዘመተ::አንዳንዴ:ቁጭ:ብዬ:ስለ:ወያኔ:ሳስብ:ወያኔና:መጥፎ:ምጣድ:አንድ:ይመስሉኛል - ሁለቱም:አይሰሙም::

የኢትዮጵያ:ጦር:በኢትዮጵያ:መንግስት:ትዕዛዝ:በአገር:ዉስጥም:ሆነ:ከአገር:ዉጭ:ግዳጁን:ሲወጣ:ወጪዉን:የሚሸፍነዉ:መለስ:ዜናዊ:ሳይሆን:የኢትዮጵያ:ህዝብ:ነዉ::በየተላኩበት:አቅጣጫ:እየሄዱ:የህይወት:መስዋዕትነት:የሚከፍሉት:ጀግኖች:ከህዝብ:ዉስጥ:የወጡ:የህዝብ:ልጆች:ናቸዉ::በዚህ:ሀቅ:ከተስማማን:መለስ:ዜናዊ:የኢትየጵያን:ሰንደቅ:አላማ:ያነገበ:ጦር:ለግዳጅ:ከመላኩ:በፊት:የህዝብን:ፈቃድ:ጠይቆ:ማግኘት:ይኖርበታል::ኢትዮጵያን:የሚመራ:ሰዉ:የራሱን:ክብርና:ዝና:ከኢትዮጵያዊነት:በላይ:የሚመለከት:ከሆነ:ክብርም:ኢትዮጵያዊነትም:አይገባዉም::መለስ:ዜናዊ:ህዝብን:ከመስማትና:ካለመስማት:ከእዉነትና:ከዉሸት:አንዱን:መምረጥ:ይኖርበታል፤ህዝብን:መስማት:ከዉሸት:አለመስማት:ደግሞ:ከእዉነት:ጋር:አብረዉ:ሊሄዱ:አይችሉም::

በ1999ዓም:በታንክና:በብረት:ለበስ:መኪናዎች:ታጅቦ:በማን:አለብኝነት:ወደ:መኻል:ሶማሊያ:የዘለቀዉ:የወያኔ:ጦር:ዛሬ:መኻሉ:ዳር:ሆኖበት:ደብቁኝ:እያለ:ነዉ::ሠላምን:ለማስከበር:በሚል:ሰበብ:ሳይጋበዝ:ወደ:ሶማሊያ:የገባዉ:የወያኔ:ሠራዊት:እንኳን:የሶማሊያን:ሠላም:ሊያስከብር:እየሮጠ:የገባበትን:ጎዳና:ሠላም:ማስከበር:ተስኖት:የሀፍረት:ሸሸቱን:የተያያዘዉ:በባህር:ለይ:ነዉ::ጦርነት:የሶማሊያን:ችግር:ያባብሰዋል:እንጂ:አይፈታዉም:ብለዉ:ብዙ:አርቆ:አስተዋይ:ኢትዮጵያዉያን:ቢናገሩም:ወያኔ:ገሚሱን:የአገር:ፍቅር:የሌለዉ:ገሚሱን:ደግሞ:አክራሪ:"ዳያስፖራ" እያለ:በማጥላላት:በፈፀመዉ:የክህደት:ስራ:ብዙ:ወጣቶችን:ለሞት:ዳርጓል::ስልታዊ:ማፈግፈግ:ካልሆነ:በቀር:ጠላት:ጀረባዉን:አይቶት:የማያዉቀዉ:የኢትዮጵያ:ጦር:ዛሬ:የወያኔ:መሪዎች:በፈፀሙት:ግዙፍ:የፖለቲካ:ስህተት:የተነሳ:አላማዉን:ከግቡ:ሳያደርስ:እግሬ:አዉጭኝ:ማለት:ጀምሯል::ነገሩእራስን:ማታለል:ሆነ:እንጂ:እንኳን:እንደ:ወየኔ:አይነቱ:ከተራበ:ህዝብ:ላይ:በተቀማ:ገንዘብ:መሳሪያ:ሸምቶ:የሚዋጋ:መንግስት:ይቅርና:በቁሳዊ:ሐብቷና:በምትሠራቻቸዉ:መሳሪያዎች:ጥራት:የዓለማችን:ቁንጮ:የሆነችዉ:አሜሪካም:ሶማሊያ:ዉስጥ:ገብታ:የፈየደችዉ:ፋይዳ:የለም::ለዚህም:ነዉ:የአዲስ:አበባዉን:ሞኝ:ባወጣህ:ያዉጣህ:ብላ:አፉን:በዶላር:ሞልታ:የላከችዉ::ሞኞ:የሚገባዉ:ቢሆን:ኖሮ:ኢትዮጵያ:የሚዘምት:ሠራዊት:ታጣ:እንደሆነ:ነዉ:እንጂ:የአሜሪካ:ዶላርማ:ማለቂያም:የለዉ::

በቅርቡ:አቶ:መለስ:ተቃዋሚ:ፓርቲዎች:ለፓርላማዉ:ላቀረቡት:ከሶማሊያ:መዉጪያ:የግዜ:ሠሌዳ:ጥያቄ:የሰጡት:መልስ:እጅግ:አወናባጅ:ነበር::አቶ:መለስ:በአንድ:በኩል:ጥያቄዉን:ሙሉ:ለሙሉ:ዉድቅ:ሲያደርጉ:በሌላ:በኩል:ደግሞ:ጦራቸዉን:ብዙም:ሳይቆበቅርብ:ቀን ከሶማልያ:እንደሚያስወጡ:ተናግረዋል:: ምንም:ይሁን

ምን:ከተቃዋሚ:ጎራ:የሚሰነዘር:ሀሳብ:እንደ:ኮሶ:የሚመራቸዉ:አቶ:መለስ:ችኮነት:የተፈጥሮ:በሽታ:ሆኖባቸዉ:ነዉ:እንጂ:"በጥቂጥ:ቀናትና""በሚቀጥለዉ:ወር"የሚል:ዝባዝንኬ:ዉስጥ:ከመግባት:አንዱኑ:ተቃዋሚዎች:ያቀረቡትን:ከሶማሊያ:መዉጪያ:የግዜ:ሠሌዳ:ጥያቄ:ቢቀበሉ:ያምርባቸዉ:ነበር::

ነገሩ:ጅብ:ከሄደ:ዉሻ:ጮኸ:ሆነ:እንጂ:ከወዲሁ:የተቃዋሚዎችን:ምክር:ሰምተዉ:ቢሆን:ኖሮ:አቶ:መለስ:ሶማሊያ:ገብተዉ:እንዲህ:ግራ:አይጋቡም:ነበር::ለመሆኑ:ወያኔ:ጦሩን:ወደ:ሶማሊያ:ያዘመተዉ:ለምንድነዉሽብርተኞችን:ለመዋጋት:ከሆነ:ከሽብርተኞች:አንዱ:እራሱ:ወያኔ:ነዉና:ዉግያዉን:ከራሱ:መጀመር:ነበረበት::ሶማሊያ:ዉስጥ:ሠላምን:ማስፈን: ከሆነም:ሰበቡ:ወየኔ:ሠላምን:እንኳን:በጦርነት:በ"ሠላማዊ" መንገድም: ማምጣት:የማይችል:ፀረ:ሠላም:ቡድን :ነዉ:: ወያኔና: ጀሌዎቹ:እንደሚየቅራሩት:የሶማሊያዉ:ጉዞ:የኢትዮጵያን:ብሔራዊ:ደህንነት:ለማስጠበቅ:አይደለም፤ቢሆንማ:ኖሮ:በምስራቅ:የአገርን:ደህንነት:የሚያስጠብቅ:ቀመንግስት:በሰሜን:የአገርን:አንድነት:አይንድም::

ለዚህ:ጽሁፍ:መንደረደሪያ:እንዲሆነኝ:የሰሞኑን:የወያኔ:ከሶማሊያ:ሽሽት:በመነሻነት:መርጬ:ነዉ:እንጂ:ወያኔ:በኢትየጵያ:አንድነትና:በህዝቦቿ:ለይ:የፈፀመዉ:በደል:ተዘርዝሮ:የሚያልቅ:አይደለም፤ዋና:ዋናዎቹን:መጥቀስ:ካስፈለገ:በ1993ዓም፤ጀግኖች:ኢትየጵየዉያን:በደማቸዉ:ነፃ:ባወጡት:መሬት:ላይ:ተደራድሮ:ኢትዮጵያን:የአሸናፊ:ተሸናፊ:አድርጓታል፤ኢሳያስ:አፈወርቅን:ጨምሮ:የብዙ:አገር:መሪዎችን:ባስገረመ:መልኩ:ኢትዮጵያ:የባህር:በር:አያስፈልጋትም:ብሎ:አገራችንን:በዓለም:ላይ:የባህር:በር:የሌላት:ትልቋ:አገር:አድርጓታል፤በቅርቡ:ከሰሜኑ:የአገራችን:ክፍል:መሬት:ቆርሶ:ለሱዳን:በመስጠት:በጀግኖች:አባቶቻችን:ደም:ቀልዷል::

ወያኔ:ወደ:ኢትዮጵያ:የፖለቲካ:መድረክ:ብቅ:ሲል:ለኢትዮጵያ:ህዝብ:እርግጠኛ:ሆኖ:ከተናገራቸዉ:ነገሮች:አንዱ:ኢትዮጵያ:ዉስጥ:ታይቶ:የማይታወቅ:የኤኮኖሚና:የፖለቲካ:ለዉጥ:እንደሚያካሄድ:ነበር::ዛሬ:ከ170መታት:በሗላ:የኢትዮጵያ:ህዝብ:ለወያኔ:አስረግጦ:መናገር:የሚፈልገዉ:ነገር:ቢኖር:ወያኔ:ኢትዮጵያን:ከመለወጡ:በፊት:እሱ:እራሱ:ወደ:ኢትዮጵያዊነት:መለወጥ:እንዳለበት:ነዉ::የወያኔዉ:ሹም:አቶ:መለስና:ፓርቲያቸዉ:ሥልጣን:ላይ:በቆዩባቸዉ:0መታት:የወሰዷቸዉ:እርምጃዎችና:ለኢትዮጵያ:ህዝብ:ያሳዩት:የተሞለቀቀ:ፀባይ:ኢትዮጵያዊነት:ቀርቶ:የኢትዮጵያዊነት:ጠብታም:ያለበት:አይመስልም::እንደአፍራሽነቱ፣እንደ:ፀባዩና:እንዳሠራሩ:ከሆነ:ወየኔ:አገርን:የመሠለ:ዉስብስብ:ክስተት:ቀርቶ:ዝርክርኩ:የወጣዉን:የራሱን:ጓዳ:እንኳን:ለመለወጥ:ብቁ:አይደለም::

ኢትየጵያዊነታችንን፡ከሚፈታተኑት፡ጨቅላ፡የወያኔ፡አስተሳሰቦች፡አንዱ፡እኛ፡የሚናገር፡አፍ፡ያለን፡እነሱ፡ደግሞ፡የሚሰማ፡ጆሮ፡ያላቸው፡አይመስላቸውም።በቻ፡አይደደለም፡የህዝብን፡ቃልኪዳን፡ለዘነጋው፡ፓርላማም፡ጭምር፡ነው።ወያኔዎች፡እንደ፡እኔው፡ሰብዓዊ፡ፍጡር፡ናቸውና፡ጥቂትም፡ቢሆን፡ይሰማሉ፥ብዬ፡ስለማምን፡አንድ፡ላሳስባቸው፡የምፈልገው፡ጉዳይ፡አለ።ግለኝነት፣ምክር፡አለመስማትና፡እኔ፥ብቻ፡ባይነት፡እንኳን፡ወያኔን፡ያክል፡ግዙፍ፡ፍጡር፡የጨካይቱን፡ቀበሮ፡ሳይቀር፡ነብር፡ነኝ፡የሚያሰኝ፡አሳሳችና፡ጎጂ፡ባህሪይ፡ነው።ስለሆነም፡ወያኔ፡ለእኔ፡ሳይሆን፡ለእኛ፣ለአንተ፣ሳይሆን፡ለእናንተ፣ጎጥ፡ሳይሆን፡አገር፡ከሚባሉ፡ሰፋ፡ያሉ፡አገር፡ገንቢ፡ፅንሰሳቦች፡ጋር፡ቢተዋወቅ፡ለሱ፡ለራሱም፡ለኢትዮጵያም፡ይበጃል።

መለስና ኩባንያው የተያያዙት ሃገር መግደል ነው:: "አባት የሞተ እንደሁ በሃገር ይለቀሳል:: ሃገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል" እያሉ እናቶቻችን እያነቡ ነው:: ማነው እምባቸውን ለማበስ የሚነሳ? ማነው ለቅሶው ይቁም የሚላቸው?

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## "ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ይኖራል ብዬ አላምንም"እና ማሪያ ጎሜዝ

ከገጽ 1የዞረ

**የሮ፡** አይ.ሲ.ዩ. የኢትዮጵያ ግዛት የሆነውን ኦጋዴንን እውስዳለሁ ብሎ አውጆ ነበር። በርግጥም የሽግግሩ መንግስት ያን ይአህል መሰረት አይኖረው ይሆናል፤ ነገር ግን ያ አይ.ሲ.ዩ የቀሰቀሰው ስጋት ከድሮ ጀምሮ የነበረና ከዚህ በፊት ኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት የሄዱበት ጉዳይ ነው። ይህ ከግምት ውስጥ ሲገባ የኢትዮጵያ ጣልቃ ገብነት ስህተት ነው?

**እና ጐሜዝ፡** አዎን በኔ አመለካከት ስህተት ነው፤ ደግሞም ለዚህ ወረራ እና ሶማሊያ ውስጥ ለሚካሄደው ጦርነት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ይህ መንግስት ኦጋዴን ውስጥ እያካሄደ ስላለው ከፍተኛ ጭቆናም ነው። እንዳዉም ሁኔታው ቁልቁል ከመውረዱ የተነሳ የኦጋዴንን ህዝብ ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄ እያባባሰው ነው። ይህ የኔ ጉዳይ ባይሆንም...ኢትዮጵያዉያን ዴሞክራቲክ እና አንድ ለሆነች ኢትዮጵያ ለመታገል መስማማት ያለባቸው ይመስለኛል። ያ አሁን ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ከዛ በኋላ፣ አለመግባባቶችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው፣ ያሉበትን የተለያዩ ሁናቴዎች፣ እያንዳንዱ ክልል ወደፊት እንዴት እንደሚቀጥል፣ ወይም እንደ ኦብነግ ያሉት አንዳንዶች መገንጠል እንኳ ቢፈልጉ፤ ያ ኋላ የሚደረስበት ነገር ነው። በሰላማዊ መንገድ ሊደረስበት የሚገባ ነገር ነው፤ በኢትዮጵያ የሚኖረው መንግስት ዴሞክራቲክ ከሆነ። እኔ አሁን ሁኔታውን እንደማየው ከሆነ ማንም ወደፊት እየተራመደ አይደለም። በኦጋዴን ውጊያ እንዳለ አውቃለሁ፤ ነገር ግን እውነታው ያ ውጊያ ከዚያ አካባቢ አለመውጣቱ ነው፤ ደግሞም ከትጥቅ ትግሉ ባሻገር የፖለቲካውን ትግልም ማሰብ ይበጃል።

**የሮ፡** የኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ ባለበት ተገትሮ ቀርቷል። መፍትሔው ምን ይመስሎታል?

**እና ጐሜዝ፡** ምንም አንኳ ይህ ለኢትዮጵያዉያን ህመም የሚቀሰቅስ ነገር ቢሆንም፣ የድንበር ኮሚሽኑ ባድመን በተመለከተ ያስተላለፈውን ውሳኔ መቀበል አለባቸው። ከኤርትራ ጋርም የተለየ ግንኙነት ለመፍጠር መሞከር አለባቸው። ኢትዮጵያ ትልቁ የሃላፊነት ድርሻ ቢኖራትም ይህ ኤርትራንም ይመለከታል። በኤርትራ ያለው አገዛዝም በጣም ጨቋኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ከኢትዮጵያ ጋር ያለው የጦርነት ሁኔታ እንዲቀጥል እያደረገና ባካባቢው ባሉ የተለያዩ ችግሮች ውስጥ ጣልቃ እየገባ ነው። ነገር ግን በኔ እምነት ኢትዮጵያ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ለመቀበል የገባችውን ቃል አለመፈጸሟ አይን ያወጣ ጥሰት ነው፤ በዩ.ኤስ. መንገስት የሚመራው የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዝምታና ኢትዮጵያ ለኮሚሽኑ የገባችዉን ቃል እንድትፈጽም ግፊት አለማድረጉም አይን ያወጣ ነው። አሁን ያለዉንም የጦርነት ሁኔታ እንዲኖር ያደረገው አንዱና ዋናው ምክንያት ያ ነው።

**እና ጐሜዝ፡** በመጀመሪያ፥ እኔ ተቃዋሚ ቡድኖችን አላበረታታም። ያ የኔ ጥያቄ አይደለም...በምን መንገድ ዴሞክራሲን ማምጣት እንዳለባቸው መወሰን ያለባቸው ኢትዮጵያዉያን ናቸው። እናም በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የተለያዩ ዘዴዎችን አንድ ላይ መጠቀም ያስፈልግሃል። ነገር ግን፥ እኔ የትጥቅ ትግልን አላበረታታም፤ ምንም እንኳ አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን ቡድኖች እሱን ሊመርጡ የሚችሉበትን ምክንያት ብረዳም። ያ በንዲህ እንዳለ፥ እኔ የተናገርኩት ነገር ስለ ትጥቅ ታጋዮች ወይም ስለ ሰላማዊ ተቃዋሚዎች አልነበረም። ያንን ዓረፍተ ነገር የተናገርኩት ባንድ ድርጅት ጥያቄ ስለቀረበልኝ ነው...ይህ ድርጅት፣ ዲ.ኤል.ኤ ፓይፐር፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን፣ ሌሎች የተቃዋሚ አመራሮችንና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን ሃገር ውስጥ መስራት ሲችሉ ለምን ከውጪ እንደሚሰሩ ሲጠይቅ ነበር። እሱ [ብርሃኑ] መልሱን ከሰጠ በኋላ እኔም ተጨማሪ አስተያየት ሰጠሁ፤ ያም አስተያየት የኔ ሃገር ፖርቹጋል በአምባገነን መንግስት አገዛዝ ስር በነበረችበት ጊዜ፣ ሃገር ውስጥ ሁለገብ በሆነ መንገድ - ማለትም ህጋዊም ሚስጥራዊም በሆነ መንገድ - የታገሉ ብዙ ሰዎች ነበሩን የሚል ነበር። ነገር ግን ሀገር ውስጥ ሊኖሩ ያልቻሉ፣ በዳያስፖራ በስደት የነበሩ እና ከውጪ ሆነው ሲሰሩ የነበሩ ብዙ ሰዎችም ነበሩን። የነዚህ ሃይሎች ሁሉ ድምር ነው ከውጪና ከውስጥ ሆኖ ለዴሞክራሲ እየሰራ አምባገነኑን መንግስት በመገልበጥ ዴሞክራሲን ለማስፈን ስኬታማ የሆነው። እና ያንን የተናገርኩት ከዲ.ኤል.ኤ. ፓይፐር የመጡት ሰዎች ከኢትዮጵያ ውጪ በስደት የሚገኘው ዳያስፖራ፣ ከኢትዮጵያ ለመልቀቅ የተገደዱት ለአገራቸው ዴሞክራሲእንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተቀባይነት የላቸውም የሚል አመለካከት ሲገልጹ ለነሱ ምላሽ ለመስጠት ነው። እኔ እንደሚመስለኝ የኢትዮጵያው ዳያስፖራ

ሊጫወተው የሚችለው በጣም አስፈላጊ ሚና አለ፤ እናም በስደት ያሉ የኢትዮጵያ መሪዎች እነሱን ለማሰባሰብ፣ እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ቅስቀሳ ለማድረግ፣ በተለያዩ መንገዶች በሰላም የማደራጀት ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። በተለይም ሚዲያዉን ለማደራጀትና ወደ ኢትዮጵያ ለማስተላለፍ፣ እንዲሁም ሃይልን አሰባስቦ አምባገነኑን መንግስት ለማስወገድ።

**የሮ፡** አሁን እራሱን አንድነት ብሎ የሰየመው ቅንጅት ከ2002 ምርጫ እራሱን ማግለል አለበት?

**እና ጐሜዝ፡** የመለስ አገዛዝ በስልጣን አስካለ ድረስ እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ አላምንም። እኔ እንደሚመስለኝ፣ የ97ቱ ልምድ እንደሚያሳየን፣ ያ ሁሉ ቃል ከተገባ በኋላ፣ ያ ሁሉ ወሬ ከተወራ በኋላ፣ አቶ መለስ ዜናዊ የገዢውን ፓርቲ ዕድሜ ለማራዘም በግልጽ ምርጫውን ከማዛባትና ከመስረቅ ወደ ኋላ አላለም። የተደረገው ምርጫ በትንሹ መስፈሪያ እንኳ ዴሞክራሲያዊ እና ፍትሓዊ ነበር ብዬ አላምንም። ስለዚህም ይህ አገዛዝ ነፃና ፍትሓዊ የሆነ ምርጫ ያካሂዳል ብዬ አላምንም። በኢትዮጵያ ነፃና ፍትሓዊ የሆነን ምርጫ ላማካሄድ የሽግግር መንግስት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ።

**የሮ፡** የትጥቅ ትግል ከሌለ፣ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር መምጣት የሚችለው አሁን ባለው መንግስት በኩል ሳይሆን አይቀርም። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ስላለበት ሁኔታ የተናገሩትንና ይህንን መንግስት የገመገሙበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ተስፋ የለውም ማለትዎ ነው?

**እና ጐሜዝ፡** አይ፥ ተቃራኒውን። ይህ መንግስት ለዘላለም በስልጣን ላይ አይቆይም። ማንኛውም አምባገነናዊ አገዛዝ ስልጣን ላይ ለዘላለም አይቆይም። በኔ አገር አርባ ስምንት አመት ወሰደ...በመጨረሻ ግን ሃይላችንን አሰባስበን አምባገነናዊውን ስርዓት ለማስወገድ ችለናል። በኢትዮጵያው የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ ላይ ግን ይህ ከዛ በጣም ባጠረ ጊዜ ውስጥ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ይህ ግን የሚወሰነው በኢትዮጵያዉያን በአንድነትና በሁለገብ አቅጣጫ፤ ማለትም በፖለቲካ፣ በባህል - በሁሉም ዘዴ፤ እራሳቸውን ከዚህ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት፤ በሚያደርጉት ትግል ነው። ይህ አገዛዝ ሊወድቅባቸው የሚችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። ግዴታ በትጥቅ ትግል መሆን የለበትም። እሱ አንድ መንገድ ነው፤ ግን ብቸኛው መንገድ አይደለም። በኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ በህዝቦች የኑሮ ሁነታ እና በመሳሰሉት መንገድ ሊወድቅ ይችላል። ብዙ ብዙ መንገዶች አሉ፤ ለማንኛውም ግን፥ ይህ መንግስት ሲወድቅ አገሪቱን ለነፃና ፍትሓዊ ምርጫ የሚያዘጋጅ የሽግግር መንግስት ለኢትዮጵያዉያን ያስፈልጋቸዋል። ወይ በስምምነት ወይም በኃይል ተገፍቶ፤ ይህ [የዚምባብዌ] መንግስት ወደ መጨረሻው አቅራቢያ እንደሆነ ግልጽ ነው። እናም ምርጫ ከመደረጉ በፊት ያንን ምርጫ የሚያካሂድ የሆነ የሽግግር መንግስት ሊኖር ይገባል። እኔ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እንደሚቻል ጠንካራ አማኝ ነኝ። ደግሞም ብዙዎች ከሚገምቱት ባጠረ ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ያ የሚወሰነው የኢትዮጵያ ኃይሎችና ዜጎች ዴሞክራሲንና የኢትዮጵያን አንድነት ማዕከላዊ ዓላማው ባደረገ አጀንዳ ዙሪያ መሰባሰብ በመቻላቸው ላይ ነው። ከዚህም አኳያ የግንቦት 7 ንቅናቄ መመስረቱ በጣም ተስፋ እንደሰጠኝ ልናገር እፈልጋለሁ፤ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ወደ አውሮፓ ፓርላማ መጥቶ ያብራራው አጀንዳም በጣም ተስፋ ሰጪ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ሁሉንም ኢትዮጵያዉያን ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ባንድነት ለማሰባሰብ ከተሳካላቸው፣ ብዙዎች ከሚገምቱት ባጠረ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያዉያን ይህ ባገራቸው ሲሆን ያያሉ የሚል ስሜት ይሰማኛል። ይህ በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ተከስቷል። ይህ በኔ አገር ተከስቷል። እጅግ በጣም የባሰ አስቸጋሪ በነበረበት በደቡብ አፍሪካ ተከስቷል። በምስራቅ አውሮፓ ተከስቷል። በኢትዮጵያም በዕርግጠኛነት ይከሰታል። ያንንም ዴሞክራሲ ከሁሉም ጋር ሆኜ ለማክበር ወደ አዲስ አበባ እንደምመለስ እርግጠኛ ነኝ።

**የሮ፡** በዚህ ቃለ ምልልስ ስለተካፈሉ በጣም አመሰግናለሁ።

**እና ጐሜዝ፡** ምንም አይደል።